**International Ethiopian Woman Organization IEWO**
**ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ)**

**IEWO, 1515 South 4th street #1801, Minneapolis, MN 55454, USA**




# ብርቱኳን ትፈታ




ብርቱኳን ሚደቅሳ የድርጅትዋ የአንድነት ለዲሞክራሲና የፍትህ ፓርቲ መሪ የሆነች ሴት በአገርዋ ኢትዮጵያ የህግ የበላይነት ባለመኖሩ እነደ እልፍ አእላፍ ታሳሪዎች በእስር ቤት ስትማቅቅ በመቆየትዋ የጤና መታወክ ችግር ደርሶባታል።

ብርቱኳን እናትዋን ህክምና ማግኘት እንዳልቻለች ስትነግራቸው የሰሙ ወታደሮች ወድያው ለያዩዋቸው። እናትየዋ እድሜቸው የገፋ በመሆኑ፣ ዋናዋ የጉዳዩ ተከታታይ የሆነች እህትዋ እስር ቤት ገብታ እንዳትጠይቃት ታግዳለች። የብርቱኳን እናት ወ/ሮ አልማዝ ገ/እግዚአብሐር የልጅ ልጃቸውን የሚያሳድጉ ሲሆኑ በቅርቡ በVOA በኩል ልጃቸው በእስር ቤት የገጠማትን የጤንነት ችግር መፍትሔ ታገኝ ዘንድ ተማጽነዋል።

ስመ ጥፉ አምባገነን ሟለስ ዜናዊ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ማንቋሸሽ የለመደበት በመሆኑ፣ አሁንም የብርቱኳንን ጤንነት በሚመለከት ሲጠየቅ ጭራሽ እስር ቤቱ ተስማምቷት ወፍራለች በማለት አሽፏል። ኢትዮጵያዊያን ዜጎች የዚህን ብልግና፣ እብሪትና ድንቁርና የተላበሰውን ሰው ማጋለጥ አለባቸው።

ዓኢሴድ /IEWO አያት የሆኑትን የብርቱኳን እናት፣ እህትዋን ብሎም ትንሽዋ ልጅዋን የሶስት ትውልድ ሴቶች በሆኑት ወገኖቻችን ላይ የሚደርሰውን ኢሰብአዊ ጭቆና የተሞላበት ድርጊት ይቃወማል ከጎናቸውም ይቆማል። በተመሳሳይ ሁኔታ ወስጥ የሚገኙ ሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ወገኖቻችንን እያሰብን በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ግፍና መከራ እንዲያበቃ ድምጻችንን ከፍ አርገን ማሰማት አለብን እንላለን።

ለሁሉም የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ብሎም የሰብአዊ መበት ተቋማትን የመበት ማፈግን እንዲቃወመና እንዲያወግዙ ዓኢሴድ/IEWO ጥሪ ያደርጋል። ብርቱኳን መደቅሳም በአስቸኳይ ህክምና ማግኘት ይገባታል እንላለን።

**ብርትኳን ትፈታ !!!!**
**ሁሉም የፖልቲካ እስረኞች ይፈቱ !!!!**
**ደበዛቸው የጠፉ እስረኞች ሁኔታም ይነገር !!!!**

www.aesed.org

aesed.iewo@gmail.com